# በአንድ ልሳን የሚቀነቀነው "ቤተሰባዊ" ዜማ

**ተክሌ መረሳ 11-22-14**

በኢፌዴሪ የመንግስት ኮሙኒኬሽን ጉዳዮች ጽህፈት ቤት ኃላፊ ሚኒስትር አቶ ሬድዋን ሁሴን በቅርቡ በወቅታዊ ሀገራዊ ጉዳዩች ዙሪያ ከጋዜጠኞች ጋር ባደረጉት ቃለ-ምልልስ የሀገራችንን ስም ጥላሸት ለመቀባት የሚባትሉ ፅንፈኛ ኒዮ-ሊበራል ሃይሎችን አስመልክተው የተናገሩትን አባባል ለዛሬው ፅሑፌ ማሟሻ ላደርገው ወደድኩ።

ሚኒስትሩ እንዳሉት አክራሪ ኒዮ-ሊበራል ሃይሎቹ በስም የተለያዩና የሚያወጡት የመግለጫ ወቅቱ የተለያየ ቢሆንም፤ የሚያወሩትና የሚደጋግሙት አንድና ተመሳሳይ ጉዳይ ነው። የአንድ ቤተሰብ መግለጫ ነው። አዎ! ተቋማቱ ስማቸው ይለያይ ካልሆነ በስተቀር እንደ በቀቀን የሚደጋግሙት አንድና ተመሳሳይ ጉዳይን ነው። ፈረንጆቹ "different day, same story" እንዲሉት ዓይነት መሆኑ ነው—በተለያየ መጠሪያ ስም፣ ቀንና አጥኚዎች የሚያቀነቅኑት ፀረ-ኢትዮጵያ "ቤተሰባዊ" ዜማ። የዘፈን ግጥሙ ልኬት አንድ የሆነ የጥላቻ ዘመቻ። ትናንት ሲፒጄ፣ ዛሬ ሂዮማን ራይትስ ዎች ነገ ደግሞ ፍሪደም ናው...ወዘተ. በተመሳሳይ ስልት ዳንኪራ የሚረግጡበት አስገራሚ ትዕይንት።

እርግጥ የአክራሪ ኒዮ-ሊበራሎች አጀንዳ ከሀገራችን አንፃር በአሳፋሪ ሁኔታ ያልተቀጣጠለበት ጊዜ የለም። እናም በዛሬው ፅሑፌ ከአክራሪ ኒዮ-ሊበራል ሃይሎች ውስጥ ራሳቸውን ሲፒጄ፣ ሂዩማን ራይትስ ዎች እና ሪፖርተርስ ዊዝ አውት ቦርደርስ... እያሉ የሚጠሩ የፖለቲካ ሃይሎችን ያልተሳካ ጩኸት ለመመልከት እንሞክራለን።

እስቲ በቅድሚያ ከሂዩማን ራይትስ ዎች እንጀምር። ለማንኛውም 'ለመሆኑ ሂዩማን ራይትስ ዎች ማነው?፣ ተግባሩስ?፣ በዘመቻ መልክ ኢትዮጵያን የማጥላላት ምስጢሩስ ምንድነው?' የሚሉ ሌሎች ጥያቄዎች ማንሳት የሚበጅ ይመስለኛል።

በፊት ለፊት የቁም ትርጉሜው "ሂዩማን ራይትስ ዎች " የሚለው መጠሪያ "የሰብዓዊ መብት ጥበቃን" የሚያመላክት ቢሆንም፤ ድርጅቱ ግን ላዩ ላይ ከለጠፊው ስያሜ ጋር አይተዋወቅም፡፡

ከዚህ ይልቅ 'በመጠሪያው ማንነት ጭንብል ተጀቡኖ ድብቅ ፖለቲካዊ አጅንዳን የሚያራምድ ፅንፈኛ ድርጅት ነው' የሚለው እሳቤ ይበልጥ ይስማማዋል፡፡

ክቡሩን የሰው ልጅ መብት በታዛነት ተጠልሎ የራሱን ርዕዩተ - ዓለማዊ አስተሳሰብ የራሳቸውን ነባራዊ ሁኔታ ተመርኩዘው የተለየ አማራጭን በሚከተሉ ሀገሮች ላይ በኃይል ለመጫን የሚጥረው ይህ አክራሪ ድርጅት፤ የገንዘብ ምንጩ ጆርጅ ሶሮስ የተባለ አክራሪ የኒዮ - ሊበራሊዝም ፖለቲካዊ-ኢኮኖሚ የፈጠረው ከበርቴ ነው፡፡

እነ ሚስተር ሶሮስ ዋነኛ ዓላማቸው ባለረብጣ ዶላር ያደረጋቸውን የኒዮ - ሊበራሊዝም ርዕዮተ - ዓለም ልዕልና እንዳይከስምና ማነኛውም ሀገር በዚህ አስተሳሰብ ብቻ እንዲመራ የማይፈነቅሉት ድንጋይ የለም፡፡

በዚሁ ግለሰብ ብቻ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ 100 ሚሊዮን ዶላር ልገሳ የተሰጠው ሂዩማን ራይትስ ዎች ፤ተቀዳሚ ተግባሩ በራሳቸው አቅጣጫ ማደግ በመጀመሩ ሀገራት ውስጥ የእነ ሚስተር ሶሮስ ህልም የሆነውን የቀለም አብዮት በማስነሳት ከቻለ የመንግስት ለውጥ ማድረግ፤ ይህ አልሳካም ካለው ደግሞ የመንግስታቱን መልካም ስም እንደ "አቡነ ዘ-በሰማያት" እየደጋገመ በሚያወጣው የሪፖርት ጋጋታ ማጠልሸት ነው፡፡

መዋሸትንና የሌለ ነገር ነባራዊ ሁኔታ መፍጠር እንደ መደበኛ ስራቸው የያዙት የእነዚህ የኒዮ - ሊበራሊዝም አምሳያ ቡድኖች ወሬ ፤ በምን ዓይነት የሂሳብ ቀመር የሂዩማን ራይትስ ዎች ማረጋገጫ ምንጭ ሆኖ የእንግሊዙን የልማት ትብብር መስሪያ ቤትን የመስከ ቅኝት አላደረከም፤ ከኛ በላይ አታውቅም እንዳስባለ "ለሰሚው ግራ" የሚሉት ዓይነት እንቆቅልሽ ነው፡፡

ዳሩ ግን አንድ እውነታን በእርግጠኝነት መናገር ይቻላል፡፡ ይኸውም ጽንፈኛው ተቋም በሰብዓዊ መብት ሽፋን በድብቅ የሚያራምደውን የፖለቲካ አጀንዳ የሚያሳካ መስሎ እስከታየው ድረስ የመረጃው ምንጭ ማንም ይሁን ምን ዳቦን "ድንጋይ ነው" ከማለት የማይመለስ መሆኑን ነው።

እስቲ ይህን ዕውነታ በአስረጂነት ለመመልከት፣ በአንድ ወቅት ለህዝቦች ባለው የወገንተኝነት ስሜት በዓለም አቀፉ ማህበረሰብ ከበሬታና እውቅና የተቸረውን እንዲሁም በአሁኑ ወቅት ብቸኛው የሠላም አስከባሪ ኃይል ወደ መሆን የተሸጋገረውን መከላከያ ሠራዊታችንን ስም ለማጎደፍ ወደጣረበት የቅርብ ጊዜው የፈጠራ ድርሰቱ ልውሰዳችሁ፡፡

…በወቅቱ በኤርትራ መንግስትና በአል -ሸባብ የሚታገዘው አሸባሪው ኦብነግ፣ ኦጋዴን ውስጥ በአንድ አካባቢ ዜጎችን በማስፈራራት የፈጠራ ፊልም ይቀርጻል። በዚህም ያልተቃጠሉ ቤቶችን እንደተቃጠሉ፣ ያልሞቱ ሰዎችን እንደ ሞቱ አድርጎ በማቅረብ ለሂዩማን ራይትስ ዎች ያቀርባል። ድርጅቱም ቦታው ላይ ተገኝቶ ሳያጣራ የአሸባሪውን ቡድን መረጃ እንደ አስተማማኝ ምንጭ በመውሰድ፤ 'የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት በኦጋዴን አካባቢ ሰብዓዊ መብት ጥሷል' ይላል፡፡

እንግዲህ ልብ በሉ! ይህ ተግባር የሂዩማን ራይትስ ዎች ኢትዮጵያን የማጥላላት ዘመቻ አንድ አካል መሆኑ ነው፡፡ ግና ገለልተኛ ወገኖች ሁኔታውነ ተከታትለው እንዳጣሩት፣ በጽንፈኛው ድርጅት የቀረበው ሀገራችንን የመወንጀል ሴራ መሰረተ - ቢስና በኦብነግ የተቀነባበረ መሆኑ ተደርሶበታል፡፡

ተቃጠሉ የተባሉት ቤቶች በተጨባጭ ቦታው ላይ እንደሚገኙ እንዲሁም ሞተዋል የተባሉ ሰዎችም "ኸረ አለን፣ ለምን እንሞታለን? የሰይጣን ጆሮ አይስማው!" እያሉ ምስክርነታቸውን ሰጡ፡፡ ሂዩማን ራይትስ ዎች ግን እነሆ አሁን ድረስ በጨበጣ መረጃ "ካፈርኩ አይመልሰኝ" እያለን ነው -"የቅሌት ቀን አይመሽም" ይሏል እንዲህም አይደል?...

የአክራሪው ኒዮ - ሊበራል ድርጅት ፀረ - ኢትዮጵያ አቋም በዚህ ብቻ የሚያበቃ እንዳይመስላችሁ፡፡ በቅድመና ድህረ - ምርጫ 2002 ወቅቶችም፣ ሲያሻው "100 ተፅዕኖ መፍጠሪያ መንገዶች"፣ በል ቢለው ደግሞ "የእርዳታ እህል ለፖለቲካ ፍጆታ እየዋለ ነው" በማለት የተለመደ የውሸት ሪፖርቶቹን አዝንቧል– ሀገራችን ውስጥ የቀለም አብዮት ለመፍጠር የሚያስችል ምህዳር አለመኖሩን ሲያረጋግጥ፡፡

በወቅቱም የመረጃ ምንጮቹ ከድርጅቱ ትርፍራፊ ለመለቃቀም የሚቋምጡትና "አንጋሽ" ፍለጋ በየኤምባሲው የሚዞሩት የመድረክ አመራሮች ነበሩ – ሰሞነኛውን በድርጅቱ አዝማችነት የተወጠነውን የቢቢሲ ዘገባን ያረጋገጡለት ጭምርም፡፡

ታዲያ እነዚህ ግልጽ የሆኑ የድርጅቱ ጣልቃ ገብነቶች የሚያመላክቱት፣ ሂዩማን ራይትስ ዎች መንግስት የመቀየር ቀቢጸ - ተስፋን ያነገበ ፖለቲካ አራማጅ ድርጅት እንጂ፣ ለሰብዓዊ መብት ጥበቃ ጋር የሚያገናኘው ምንም ዓይነት ነገር የሌለው መሆኑን ነው፡፡

ይሁንና እዚህ ላይ ይህ 'ድርጅቱ በአፍሪካም ይሁን በሀገራችን ላይ መቋጫ የሌለውን የኒዮ - ሊበራሊዝም ፕሮፓጋንዳን ለዚህ ተግባር ተብለው በተዘጋጁት እንደ ቢቢሲ፣ ቪኦኤ ወዘተ. ዓይነት ሚዲያዎች የሚረጭበት ምስጢር ምንድ ነው?' የሚል ጥያቄ ማንሳት አግባብ ይመስለኛል፡፡

ቀደም ሲል ለመጥቀስ እንደሞከርኩት፣ ጽንፈኛ ኒዮ -ሊበራሉ ተቋም ራሱ ከሚያራምደው ርዕዮት ውጪ የትኛውም አህጉርና አህገር የራሱን አስተሳሰብ እንዲከተል አይፈቅድም፡፡ በተለይም አፍሪካና ሀገሮቿ ምንጊዜም የምዕራቡ ዓለም ጥገኛ ሆነው እንዲኖሩ የሚፈልግ ተቋም ነው፡፡

ለዚህም ነው 'ለምን ከኛ አመለካከት ውጪ አደጋችሁ?' በማለት አፍሪካንና ፈጣን ዕደገቷን የማናናቅ አባዜ ተጠናውቶት የቤተክርስቲያን ስዕለት ያለበት ይመስል በየጊዜው በቀጥታ ሪፖርት ጋጋታ እና በእጅ አዙር ጋዜጠኝነት አስገራሚ ልቦለዳዊ ትወና በማካሄድ ላይ የሚገኘው ፡፡

እርግጥ ሀገራችን በራሷ ልማታዊ ዴሞክራሲያዊ አስተሳሰብ እየተመራች በአሁኑ ወቅት ፈጣንና ተከታታይ ዕድገት ማስመዝገቧ 'ከኒዩ - ሊቢራሊዝም በስተቀር ሌሎች አማራጮች ለዕድገት አያበቁም' ብሎ የሚያስበውን አክራሪ "የፖለቲካ ድርጅት" በአያሌው ብስጭት ውስጥ እንደከተተው እሙን ነው፡፡

ለዚህም ነው በወቅቱ ለቢቢሲው ዘገባ ምላሽ የሰጡትን ሚኒስትር ሚቼልንና የእንግሊዝ መንግስትን እጅግ ጠንካራ በሆኑ ቃላት እየደነፋ የወረፈው፡፡ ይሁንና "የሽሮ ድንፋታ ውኃ እስኪገባበት ድረስ ነው" እንዲል ታታሪው ህዝባችን፤ የሂዩማን ራይትስ ድንፋታ ሃቅን ተሻግሮ የትም የሚደርስ አይደለም፡፡

ከዚህ ይልቅ ድርጅቱ ኢትዮጵያ ውስጥ ያለውን እውነታ ዓይኑ ላይ ያሰረውን የጥላቻ መሃረብ በመግለጥ መመልከት ያለበት ይመስለኛል። ያም ሆነ ይህ ግን የፅንፈኛው ቡድን የቁራ ጩኸት ያለ አዳማጭ በከንቱ ባክኗል። ይህ ፅንፈኛ ቡድን ሰው ቀጥሮም የሀገራችንን ስም እስካማስጠፋት የደረሰ ነው። በቅርቡ ሄለን ኤፕስተን የተባለች ግለሰብን በመቅጠር የህዝባችንን ስም ሊያጠቁር መሯሯጡ አብነታዊ ምሳሌ ነው።

ሴትየዋ ፀረ- ኢትዮጵያዊነትን ባቀነቀነችበት ሰሞነኛ አጀንዳዋ የኢትዮጵያ መንግስት ከለጋሽ ሀገሮች የሚያገኘውን ገንዘብ ያለአግባብ ለሰብዓዊ መብት ጥሰት እያዋለው መሆኑን በመደስኮር ለጋሽ ሀገራት ከዕርዳታና ከብድር እጃቸውን እንዲሰበስቡ ማስጠንቀቂያ ቢጤ ጣል አድርጋለች፡፡

በእርግጥ ፀሃፊዋ የኢትዮጵያን መንግስት ስም ለማጠልሸት ብዕሯን የመዘዘችው ሀገር ቤት መጥታ ነባራዊውን ሃቅ ስለተገነዘበች አይደለም፡፡ ይልቁንም አንዳንድ የሰብዓዊ መብት ተቆርቋሪ ነን ባዮች በሚያቀብሏት በሬ ወለደ ዘገባ ተገፋፍታ እንጂ፡፡

በተለይም ለተቋሙ ልዩ ፍቅር ያላት የሚመስለውን "ሂዮማን ራይትስ ዎች"ን እንደ ትክክለኛ እማኝ በመጥቀስ ያልዘላበደችው ነገር አለ ለማለት አያስደፍርም፡፡ "የአይጥ ምስክሯ ድንቢጥ ናት" ይላል የሀገሬ ሰው—እንዲህ ዓይነት ከህሊና ውጪ የሆነን የመጠቃቀም አሳዛኝ ድርጊትን ሲመለከት።

እናም ወይዘሮዋ የተቋሙ አገልጋይ በመሆኗ ከተቋሙ የምታገኛቸውን የሃሰት ቃርሚያዎች በማሰባሰብ ብቻ ያልተገባ ወሬ ለመንዛት መነሳቷ ብዙም የሚደንቅ አይደለም – አጀንዳዋና አጀንዳቸው ስለኢትዮጵያ መንግስት ማስረጃ የሌለው ድርሳን መከተብ በመሆኑ ሰሞነኛ ዘገባዋም የሚጠበቅ ነው፡፡

እርግጥ “ሂዮማን ራይትስ ዎችም” ይሁን አንዳንድ በሰብዓዊ መብት ስም ተጠልለው የስሶተኛው ዓለም ሀገራትን መንግስታት ስምና ዝና ለማጠልሸት ገንዘብ መድበው፣ ‘ባለሙያ’ ቀጥረው የሚራኮቱ ተቋማት ድብቅ አጀንዳ ምን እንደሆነ የሚያውቅ ያውቀዋል።

ተቋማቱ በክቡሩ ሰብዓዊ መብት ስም የሚነግዱ  የኒዩ - ሊበራሊዝም ፖለቲካዊ-ኢኮኖሚ ህልመኞች ናቸው፡፡ ድሃ ሀገራት እነሱ በሚፈልጉት መስመር ለመጠምዘዝ ፈቃደኛ መሆን ካልቻሉ ያለ የሌለን የፈጠራ ዘገባ በማጠናቀር ከለጋሽ ሀገራት ጋር ለማላተም ተግተው የሚከሰቡ የበጋ ገበሬዎች ናቸው፤ በተጠባጭ እንደታዩት፡፡

ሴትዮዋም “የሂዮማን ራይትስ ዎች” ቅጥረኛና ደቀ - መዝሙር በመሆኗ ሰሞኑን ለማራገብ የሞከረችውን የብዕር ስራዋን ይዛ ብቅ ብላለች፡፡ እኔ በግሌ የፀሐፊዋን “የሂዮማን ራይትስ ዎችን” አዳማቂነት በአሮጌ አኩፋዳ የተቀመጠ አዲስ ወይን አድርጌ ነው የምቆጥረው ፡፡ ምክንያቱም ከሴትዮዋ ስብዕና እና ተልዕኮ አንፃር ሃቁን መጠበቅ ሰማይን የማረስ ያህል የሚያስቸግር በመሆኑ ነው፡፡ ለነገሩ የሴትየዋም መልዕክት እንደ ላኪዋ የቁራ ጩኸት ሆኖ ቀርቷል።

እስቲ አሁን ደግሞ ራሱን ድንበር የለሹ የጋዜጠኞች ቡድን እያለ ወደሚጠራው ሌላኛው አክራሪ ኒዮ-ሊበራል ሃይል እናምራ። ቡድኑ በቅርቡ በሽብርተኝነት ወንጀል ተከስሰውና ጥፋተኛ ሆነው በመገኘታቸው ምክንያት ማረሚያ ቤት የሚገኙትን የውብሸት ታዬና የርዕዮት አለሙ ጉዳይ እንዳሳሰበው መግለጫ አውጥቶ ነበር።

የሁለቱ ጋዜጠኞች ለረጅም ጊዜ መታሰር “አዲሱ” መንግስት ለሚዲያ “ነፃነት” ደንታ ቢስነቱን የሚጠቁም መሆኑን ጨምሮ ያስታወቀው ቡድኑ፤ የኘሬስ ነፃነቱን ተስፋ ያሟጠጠ ሲልም መንግስትን ለማጣጣል እንዲሁም በአለም አቀፍ ተቋማትና ማህበረሰብ ዘንድ ተቀባይነትን ለማሳጣት ሞክሯል።

ግና ቡድኑ ባላቸው ጉዳዮች ዙሪያ ከመነጋገራችን በፊት፤ የሀገራትን የህግ የበላይነት በመፃረር 'ህጋችሁን ሻሩ' ለማለት የደፈረው ይህ ተቋም እንደ ስሙ ድንበር የለሽነቱ "ድንበር" የለውምን?–ድንበር የለሽ ማለትስ ወሰኑ እስከየት ድረስ ይሆን?... የሚሉ ጥያቄዎችን ማንሳት ያስፈልጋል። ለምን ቢሉ፤ ቡድኑ ራሱ የሚያከናውናቸው ተግባራት ምን ያህል ተቀባይነት የሌላቸው መሆኑን ስለሚያመላክተን ነው። እናም እኔ እስከሚገባኝ ድረስ ማንኛውም ተግባር ወሰን ወይም ድንበር አለው።

ማንኛውም አካል በየትኛውም ጊዜና ቦታ የተገደበ ነው–ባሻውና በፈለገው ወቅት እንደ እርጎ ዝንብ ጥልቅ ብሎ አንድ ጉዳይ ውስጥ እጁን ሊዶል አይችልም። ስለሆነም ዓለማችን በህግና በስርዓት የምትመራ እንደመሆኗ መጠን፤ ያለ ድንበር እንዳሻችን ልንፈነጭበት የምንችልበትን ቦታ በውስጧ ፈልገን ልናገኝ አንችልም–ሕዋ ላይ ካልሆነ በስተቀር።

ከዚህ አኳያ ድንበር የለሹ የጋዜጠኞች ቡድን ለራሱ የሰጠውም ስያሜ ይሁን የሚያከናውነው ተግባር ድንበር ያለውና የተወሰነ ነው መሆን ያለበት–ክንዋኔው ምድር ላይ እስከሆነ ድረስ። ግና ቡድኑ 'የለም እኔ ስራዬን የምከውነው በሕዋ ውስጥ ስለሆነ አንተን ምን ያገባሃል?' የሚለኝ ከሆነም፤ እርግጥም የተቋቋመበት ዓላማ የተለየ ፖለቲካዊ ጉዳይን ለማስፈፀም እንደሆነ ለመጠራጠር አልፈልግም።

በእኔ እምነት ስያሜው እንደፈለገውና በዘፈቀዳዊ አሰራር የሀገራት የውስጥ ጉዳይ ውስጥ ጣልቃ በመግባት የፈለገውን ፖለቲካዊ-ኢኮኖሚ ፍልስፍና ለማራመድ ሆን ተብሎ የተሰጠው ነው– "እምሳዬ ነሽ..." እንዳለው ዘፋኙ መንትያ ወንድሙና አክራሪው ኒዮ-ሊበራል ተቋም የሆነው ሲ.ፒ.ጄ. በማይደርስበት ቦታ አቆራርጦ በመገኘት ሀገራትን በሁለት ዱላ ለመምታት እንዲያገለግል ተደርጎ የተፈበረከ።

ያም ሆነ ይህ ግን ቡድኑ የኢትዮጵያ መንግስት ሁለቱን ጋዜጠኞች ያለጥፋታቸው መወንጀሉን "ነፃ" ፕሬስን የማፈኑን ተግባር እንደገፋበት በመጥቀስ ፍፁም ከሃቅ ርቆና እውነቱን ደፍጥጦ የሀገራችንን መልካም ገፅታ በብዕር ለማበላሸት ተውተርትሯል።

ይሁን እንጂ ሰሞኑን እርሱ የጠቀሳቸው ጋዜጠኞች አካል የሆነው የግል ሚዲያው ዓለም አቀፍ የፕሬስ ቀንን አስመልክቶ በሒልተን ሆቴል ከመንግስት ጋር ባካሄደው ውይይት

ራሱ ችግሮች እንዳሉበትና በእስከ አሁን ጉዞውም ከጋዜጠኝነት ሙያ ያፈነገጠ እንዲሁም ትክክል እንዳልነበረ አምኗል፣ራሱንም ገምግሟል፡፡

በሌላ አነጋገር "ነፃ" ፕሬሱ ችግሮች እንዳሉበት በአደባባይ እየመሰከረ፣ ቡድኑ ግን ፕሬሱ ምንም እንከን እንደማይወጣለት፣ መንግስት ግን የግል ሚዲያውን ለማዳከም ጋዜጠኞችን እንደሚያንገላታና ጣልቃ እንደሚገባ በመጥቀስ አይኑን በጨው አጥቦ ለመታበይ ሞክሯል፡፡

ሁለት እርስ በእርሳቸው የሚጋጩ አባባሎች። የግሉ ፕሬስ ችግሮቹን ቢያምንም ፣ ቡድኑ ግን 'የለም ትክክል ነበር' እያለ በፕሬሱ ስም እየተሟገተ ነው፡፡ ይህ አባባል ሌላ ትርጉም ካልተሰጠው በስተቀር ለእኔ መተላለፍ፣ አሊያም መሸዋወድ ነው። የማን አለብኝነት ድምዳሜ ነው– "ከባለቤቱ ያወቀ ቡዳ ነው" እንዲሉት ዓይነት፡፡ የድንበር የለሹ የጋዜጠኝነት ቡድን ድፍረት የኢትዮጵያ "ነፃ" ፕሬስ ፍፁም ምንም እንከን የማይወጣለት መሆኑን በአደባባይ መመስከሩ ብቻ አይደለም፡፡ የጠቅላይ ሚኒስትር መለስን ህልፈተ-ህይወት ተከትሎ የርዕዮተ - ዓለም ለውጥ አለመኖሩን መተቸቱም ጭምር እንጂ።

ይህ ደግሞ የማን አለብኝነቱን ግዝፈት ያመለክታል፡፡ እርግጥ "አዲሱ" መንግስት ምንም ዓይነት ለውጥ አለማድረጉ ቡድኑን አላስደሰተውም፡፡ ምን ዓይነት ለውጥ እንደተመኘ ባይጠቁምም ቅሉ፣ ቡድኑ ስር ነቀል ለውጥ አምሮት ነበር ወይም አምሮታል፡፡ ሆኖም ስያሜው እንደሚያመለክተው የቡድኑ ተልዕኮ የፕሬስ ነፃነትን ማረጋገጥና ለጋዜጠኞች ዋስትና የሚሰጥ ስርዓት እንዲኖር ከማቀንቀን በስተቀር የስርዓት ለውጥን መስበክ ስራው አልነበረም። ግና እንደ ሂዩማን ራይትስና ሌሎች የኒዮ-ሊበራሊዝም አቀንቃኞች ይህ ቡድንም እየተሟገተ ያለው ለጋዜጠኞች መብት ሳይሆን ለስርዓት ለውጥ በመሆኑ ተግባሬ ነው የሚለው ስራው የሚመለከተው አይደለም።

እናም ስያሜውን "ድንበር የሌለው አክራሪ የኒዮ-ሊበራሊዝም ባለሟል" በሚል ቢቀይረው ይመጥነዋል ባይ ነኝ። ያም ሆነ ይህ ግን ቡድኑ ምንም እንኳን ሥራውና ምግባሩ በሀገራት የውስጥ ጉዳይ እየገቡ መፈትፈትና የራስን ርዕዮተ- ዓለም

የሚያራምድ መንግስት እንዲመሰረት መመኘት አሊያም መወትወት ቢሆንም ፣ በገሃድ ግን የኢትዮጵያ ስርዓት አለመለወጡ እንዳላስደሰተው ማተቱ የበዛ ድፍረት ነው፡፡

በዚህ ጽሁፍ አቅራቢ እምነት ቡድኑ ኢትዮጵያ የርዮተ ዓለም ለውጥ አለማድረጓን መተቸቱና አዲሱ መንግስት /እሱ እንደሚለው/ የአቋም ክለሳ ለማድረግ ፈቃደኛ አለመሆኑን መውቀሱ የተለመደ የአክራሪ ኒዮ-ሊበራል ሃይሎች ጠርነት ነው፡፡ ይሁንና እኔ እስከሚገባኝ ድረስ ግለሰቦች በልዩ ልዩ ምክንያቶች ከሃላፊነት መነሳታቸው ያለና የሚኖር ሃቅ ነው—ዘላለማዊ ባለስልጣን አይኖርምና፡፡

እናም የታላቁ መሪያችን ድንገተኛ ህልፈት ፓርቲውንም ሆነ ሀገሪቱን አይጐዳም ባይባልም፤ ድርጅቱን የአቋም ለውጥ እንዲያደርግ ግን አያስገድደውም፡፡ አቶ መለስ በህይወት በነበሩበት ወቅት በአንደበታቸው እንደተናገሩት ኢህአዴግ እርሳቸውን ፈጠራቸው እንጂ፣ እርሳቸው ኢህአዴግን አልፈጠሩትም።

እናም የአቶ መለስ አለመኖር ፓርቲው ራሱን እንደገና የማዋቀር ወይም ቡድኑ እንደሚለው የአሰራር ለውጥ መጠበቁ ስህተት ብቻ ሳይሆን ድፍረትም ጭምር ነው። መንግስትን የመሾም፣ የመሻር፣ የመውቀስና የማወደስ መብት የኢትዮጵያ ህዝብና የኢትዮጵያ ህዝብ ብቻ እንጂ የድንበር የለሽ የጋዜጠኞች ቡድን መብት አይደለም፡፡

በመሆኑም ቡድኑ “አዲስ” መንግስት እያለ በራሱ ፍላጐት ለመጠፍጠፍ የተመኘው የምናብ ዓለም ኒዮ-ሊበራሊዝም መንግስት በሀገራችን መቼም ሊከሰት እንደማይችል ተስፋ ስለቆረጠ ነው— የኘሬስ “ነፃነት” መቀጨጨን እንደ ሰበብ አስባብ በመምዘዝ የመንግስትን ገፅታ ጭቃ ለመቀባት ደግሞ ደጋግሞ የሚወተውተው፡፡

“በነፃው” ኘሬስ ጥላ ስር ተጠልሎ የራሱን ድብቅ አጀንዳ በምድረ- ኢትዮጵያ ለመዝራትና የእጅ አዙር ቅኝ ግዛት አውድ ሀገራችን ውስጥ ለመፍጠር ተልካሻ ምክንያት እየቃረመ ፀረ-ህዝብና መንግስት አቋሙን ሣይታክት ማራገቡ አላዋጣውም። ምክንያቱም እንደ ሌሎቹ ፅንፈኛ ኒዮ-ሊበራል ሃይሎች ሁሉ ጩኸቱ ከስሟልና።

ከዚህ ፅንፈኛ ተቋም ምንም ልዩነት የሌለው ሲፒጄም እንዲሁ ጩኸቱን አሰምቷል። ረብ ያለው ነገር ባያገኝበትም። ተቋሙ በሽብርተኝነት ወንጀል ተከስሰው የፌዴራሉ

ጠቅላይ ፍርድ ቤት የስር ፍርድ ቤት የተሰጠውን ውሳኔ ያፀናባቸውን እነ አቶ እስክንድር ነጋንና አቶ አንዱዓለም አራጌን እንዲሁም ሌሎች ተከሳሾችን በተመለከተ የሀገራችንን ፍርድ ቤቶች ለማኮሰስ ጥረት አድርጓል። የተከሳሾቹን የፍርድ ሂደት በተመለከተ የሀገራችንን ፍርድ ቤቶች ነፃነትን በመደፍጠጥ በሂደቱ ጣልቃ ለመግባት ያልሞከረ ኒዮ-ሊበራል ተቋም አለ ለማለት አያስደፍርም።

በተለይም ኢትዮጵያ ውስጥ የሚከናወኑ ማናቸውም ነገሮች ትክክል የማይመስሏቸው እና ስያሜያቸውና ተግባራቸው ለየቅል የሆኑት እንደ ጋዜጠኞች መብት ተከላካይ ነኝ ባዩ ሲፒጄን፣ ሂዩማን ራይትስ ዎችንና ፍሪደም ናውን የመሳሰሉ አክራሪ ኒዮ-ሊበራል ቡድኖች፤ ከርዕዮተ-ዓለም ልዩነታቸው በመነሳት ግለሰቦቹ በተከሰሱበት የሽብር ወንጀል የስር ፍርድ ቤት (ከፍተኛው ፍርድ ቤት) የሰጠውን ብይን ጠቅላይ ፍርድ ቤቱ በማፅናቱ ሳቢያ የተለመደ ፀረ-ኢትዮጵያ መዝሙራቸውን ከማሰማት በዘለለ ማስጠንቀቂያ እስከ መስጠትም ደርሰዋል።

በተለይም አክራሪው ኒዮ ሊበራል ተቋም ሲፒጄ የሀገራችንን ፍርድ ቤቶች የአሰራር ነፃነት እጅግ በሚያስገርም ሁኔታ በመጋፋት በአፍሪካ ዳይሬክተሩ ሞሐመድ ኬይታ አማካኝነት "…ውሳኔው የሽብርተኝነትን ከባድ ወንጀል ያሳነሰ፣ በፖለቲካ ተነሳሽነት የተሰጠውን የይምሰል ፍትሕ የደገፈ እንዲሁም የኢትዮጵያን ዓለም አቀፍ ደረጃ የቀነሰ ነው።…

የኢትዮጵያ መንግስት እስክንድርን ካለ ምንም ቅድመ ሁኔታ ሊለቅ ይገባል" ብሏል። ይህ የፅንፈኛው ቡድን አባባል ቢያንስ በሶስት ምልክታዎች ሊታይ የሚችል ነው። አንደኛው የሀገራችንን የፀረ-ሽብርተኝነት ህግ ያጣጣለ ሲሆን፤ ሁለተኛው የኢትዮጵያን ፍርድ ቤቶች አሰራርን ነፃነት የሌለው አስመስሎ ማቅረቡ ነው።

ሶስተኛው ደግሞ ቡድኑ ከጋዜጠኞች መብት ጠባቂነት ወደ ሀገራት የሰብዓዊ መብት ደረጃ መዳቢነት ከመሸጋገር ባለፈ፤ ለይስሙላም ቢሆን የሚያራግበውን የስራ ገደብ ዘሎ አንድን ሉዓላዊት ሀገር በመዳፈር ማስጠንቀቂያ ቢጤ በመስጠት በሀገራችን ፍርድ ቤቶች ጥፋተኛ መሆኑ የተረጋገጠበትን ግለሰብ በአስቸኳይ እንዲፈታ ለማዘዝ መሞከሩ ነው።

ታዲያ እነዚህን ሶስት የተቋሙን ነውረኛ አባባሎች በዝርዝር ከመመልከታችን በፊት ቡድኑ ስለተሟገተለት አቶ እስክንድር ነጋ ጥቂት ግንዛቤ መያዝ አስፈላጊ ይመስለኛል። አቶ እስክንድር በምርጫ 97 ወቅት ከቅንጅት ነውጠኛ አመራሮች ጋር በማሴር ህገ-መንግስቱንና ህገ-መንግስታዊ ስርዓቱን በኃይል ለመናድ ባከናወኑት የጥፋት ተልዕኮ ተከስሰው ጥፋተኛ በመሆን ለሁለት ዓመታት መታሰራቸው ይታወሳል።

ይሁንና በወቅቱ አቶ እስክንድርና መሰሎቻቸው ዳግም በእንዲህ ዓይነቱ ፀረ-ህዝብ ስራ ውስጥ እንደማይሰማሩ ገልፀውና ከስተቱን በድጋሚ ከፈፀሙ በህግ የተበየነባቸው ውሳኔ እንዲተገበር ተማፅነው መንግስት ይቅርታ እንዲያደርግላቸው በደብዳቤ ይጠይቃሉ።

በዴሞክራሲያዊ መርህ የሚመራውና አንዱ እሴቱ የሆነውን መቻቻልን የሚያስቀድመው የሀገራችን መንግስትም፤ የእነ አቶ እስክንድርን የይቅርታ ደብዳቤ በመቀበል በህጉ መሰረት ከእስር እንዲፈቱ ይወስናል–ከጥፋታቸው ይማራሉ በሚል እሳቤ። ይሁንና ነገሩ "ያደቆነ ሰይጣን ሳያቀስ አይተውም" እንዲሉ በመሆኑ፤ አቶ እስክንድር ከእስር ከተፈቱ ወዲህ እንኳንስ ከጥፋተኝነታቸው ሊማሩ ቀርቶ ይባስ ብለው ግጭትንና ሁከትን ብሎም ግብረ-ሽበራን በሚቀሰቅሱ ተግባራት ላይ መሰማራትን ስራዬ ብለው ነው የተያያዙት።

እንዲያውም ከእስር ከተለቀቁ ወዲህ በግልፅና በተዘዋዋሪ በምርጫ 97 ወቅት የጀመሩትን የሴራ ተልዕኮ ለመተግበር ይበልጥ ባተሌ ሆነው መከረማቸውን የዚህ ፅሑፍ አንባቢ የሚዘነጋው አይደለም። እርግጥም ሰውዬው ጥራዝ ነጠቅና ሴራን የሚዶልቱ ፖለቲከኛ ስለመሆናቸው የማያውቅ ሰው ያለ አይመስለኝም፡፡ የዚህች ሀገር እና ህዝቦቿ ለውጥና ዕድገት ፈጽሞ የማያስደስታቸው፤ በጥላቻ የተሞሉ፣ ጭፍን ፖለቲከኛ መሆናቸውንም ጭምር፡፡

ታዲያ በወቅቱ ይህን የለበሱትን የጭፍን ተቋዋሚነት ማዕረግ በግልፅ ደርበውት አደባባይ ለመውጣት አልፈለጉም። ይልቁንስ ሰውዬው በሐሰተኛ ማዕረግ እንዲጠሩ ነው የከጀሉት፡፡

ለዚህም ደግሞ ተመሳሳይ አቋም ባላቸው አንዳንድ የግል ሚዲያዎች "ጋዜጠኛ፣ ተንታኝና ጦማሪ" በሚል ዕውቅና ለማግኘት ያደረጉት ጥረት እንደ አንድ ማሳያ ሆኖ ሊቀርብ ይችላል። እኔ እስከሚገባኝ ድረስ ግን አንድ ፅንፈኛና ሁከት ናፋቂ እንዲሁም ከሀገሪቱ ህግ ውጭ እንዳሻው የሚፈነጭ ግለሰብ "ጋዜጠኛ፣ ተንታኝና ጦማሪ" ነኝ ብሎ ለመናገር ብቃቱም ሆነ ድፍረቱ ያለው አይመስለኝም፡፡ ያም ሆነ ይህ ግን አቶ እስክንድር ራሳቸውን ለመደበቅ የተጠቀሙበት ዘዴ ልክ እንደ ዛሬው ተከራካሪያቸው ሲፒጄ ዓይነት ያለ ተግባራዊ ማንነት በሐሰት ስም መንቀሳቀስን ነው።

ዳሩ ግን የጋዜጠኛነት ሙያ ሰውዬው ከተዘፈቁበት የጥላቻ ፖለቲካ ገለልተኛ መሆንን ያዛል፡፡ ጋዜጠኛ ለህዝብ ጥቅም የሚሰራ እንጂ እንደ እርሳቸው በሰላም የልማት ተጠቃሚነቱን እያረጋገጠ ያለውን የሀገራችንን ህዝብ ወደ ብጥብጥና ሁከት ለመስደድ የሚሯሯጥ አይደለም፡፡ የሙያው ሥነ- ምግባርም እርሳቸው እውነትን ለመቅበር የሚያደርጉትን ዓይነት መፍጨርጨር በጽኑ የሚቃወም ነው። እናም ግለሰቡ ሙያው ከሚጠይቃቸው መስፈርቶች አንዱን እንኳን ሳይዙ ራሳቸውን "ጋዜጠኛ" ብለው ሊሾሙ አይገባቸውም። ሌሎች አጫፋሪዎቻቸውም ቢሆኑ።

እኔም ሆንኩ ድፍን የኢትዮጵያ ህዝብ የአቶ እስክንድር ነጋን ማንነት ያውቃል ብዬ የማምነው ጋዜጠኛም፣ ተንታኝም ሆነ ጦማሪ አለመሆናቸውን ነው። ለዚህ ደግሞ ማስረጃ ፍለጋ ብዙ ርቀት መጓዝ የሚጠይቅ አይመስለኝም፡፡ ምክንያቱም ግለሰቡ ባገኙት አጋጣሚዎች ሁሉ ሲያሻቸው በስማቸው፣ ደስ ሲላቸው ደግሞ በብዕር ስማቸው ተጠቅመው የሚጽፏቸው ልቦለዳዊ ትረካዎች፣ የፅልመት ውሸከታዎች… ወዘተ. ከበቂ በላይ ማረጋገጫዎች በመሆናቸው ነው፡፡

ሰውዬው ከእስር ከተፈቱ በኋላ በተቃዋሚ ቡድኖች የበጀት ድጋፍ በሚታተሙ "ጋዜጦች" ላይ በነጻ አሊያም ከፍለውም ቢሆን የሚያሳትሟቸው የፈጠራ ስራዎች ዕውነታውን ፍንትው አድርገው ያሳያሉ— የእርሳቸውን ጨለምተኝነት፣ ከሃዲነት እና እብደት። ስለሆነም በእኔ እምነት እርሳቸውን "ጋዜጠኛ፣ ተንታኝና ጦማሪ" እያለ የሚጠራ ግለሰብ ወይም ቡድን አንድም ተሳስቷል አሊያም እያላገጠባቸው ይመስለኛል።

እርግጥም መሬት ላይ ያለው ሃቅ ይህና ይህ ብቻ ነው። ግና ዕውነታው ይህ መሆኑ እየታወቀ፤ 'ሲፒጄ የሀገራችንን የፀረ-ሽብርተኝነት ህግ ለምን ለማጣጣል ከጀለ?፣ ለምን የኢትዮጵያን ፍርድ ቤቶች አሰራርን ነፃነት የሌላቸው አስመስሎ ለማቅረብ ሞከረ? ከጋዜጠኞች መብት ጠባቂነት ወደ ሀገራት የሰብዓዊ መብት ደረጃ ምደባ አፅዳቂነት ተሸጋግሮና ለይስሙላም ቢሆን የሚያራግበውን የስራ ገደቡን አልፎ አንድን ሉዓላዊት ሀገር በመዳፈር ማስጠንቀቂያ ቢጤ በመስጠት ወንጀለኛውን ግለሰብ በአስቸኳይ እንዲፈታ ለማዘዝ እንደምን ደፈረ?' የሚሉትንና ቀደም ሲል የአቶ እስክንድርን የሁከት ፈጠራ አብነታዊ ትውስታዎቹን ለማየት ስንል በይደር ያቆየናቸውን ጉዳዩች እንድናነሳ ያደርገናል።

ምንም እንኳን የሲፒጄው የአፍሪካ ዳይሬክተር ሞሐመድ ኬይታ የሀገራችን ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች የወከሏቸው አባላት የሚገኙበት ፓርላማ መርምሮ ያፀደቀውን የፀረ-ሽብርተኝነት ህግን ከድርጅታቸውም ይሁን ከራሳቸው ተግባርና ኃላፊነት ውጪ በሆነ መንገድ ለማጣጣል ቢሞክሩም፤ ሃቁ ግን እርሳቸው እንዳሉት አይደለም። በመጀመሪያ ደረጃ ሚስተር ኬይታ በአንድ ሀገር የውስጥ ጉዳይ /ለዚያውም የፍትሕ ጉዳይ/ ውስጥ ጣልቃ መግባት የሚችሉበት ህጋዊ መብት የላቸውም።

ይህ ከፍተኛ ንቀት ነው። እርሳቸው ማውራት ያለባቸው የውሸት መጠሪያቸው ስለሆነው የጋዜጠኝነት መብት ተከላካይነት እንጂ ከልዩ የርዕዩተ-ዓለም ተልዕኳቸው በመነሳት ስለ አንድ ሀገር ህግ አይደለም።

ግና ይህ የእርሳቸውም ይሁን የድርጅታቸው ገደብ እንደተጠበቀ ሆኖም ቢሆን ፤ የሀገራችን የፀረ-ሽብርተኝነት ህግ ከዓለም አቀፉ ተመሳሳይ ህጎች ጋር ልዩነት ያለው አይደለም። አብዛኛው ክፍሉም ከምዕራቡ ሀገራት እንዳለ የተገለበጠ ነው ማለት ይቻላል።

እናም ህጉም ይሁን የፍርድ ቤቶቹ ውሳኔ የሽብርተኝነትን ከባድ ወንጀል ያሳነሰም ሆነ ያገዘፈ አለመሆኑን በቅን ልቦና መገንዘብ ያስፈልጋል– የትም ሀገር ውስጥ ቢሆን

ሽብርተኝነት ያው ሽብርተኝነት ነውና። የአፍሪካ፣ የአሜሪካ አሊያም የአውሮፓ ሽብርተኝነት የሚባል ነገር የለምና።

መቼም በእነዚህ ሀገራት ውስጥ የሚገኙት ሽብርተኞች ቢሳካላቸው የሚያፈሱት የንፁሃን ሰዎችን ደም እንደመሆኑ መጠን፤ የተግባሩ አደገኛነት መለካት ያለበት ከዚህ ሃቅ አኳያ መሆኑን ሀገራችን ውስጥ የተፈፀመ አንድን ነገር ሲሰማ በውሃ ቀጠነ ማላዘን የሚወደው አክራሪ ተቋም ይስተዋል ብዬ አልገምትም።

ለነገሩ አንድ ሀገር ህግ ሲያወጣ በውስጡ ያሉትን መሰረታዊ ሃቆችን ተመርኩዞ የህዝቡን ሰላማዊ የህይወት መስተጋብር ለማረጋገጥ መሆኑን በጋዜጠኞች መብት ጠባቂነት ሽፋን የኒዮ-ሊበራል ሃይሎች ተላላኪ ሆነውና እነርሱን ወክለው በሀገራችን ላይ የውሸት ክምር የሚደረድሩት ግለሰብና ድርጅታቸው መገንዘብ ያለባቸው ይመስለኛል።

ያም ሆነ ይህ ሀገራችን ከድህነት አረንቋ ለመውጣት በከፍተኛ ትግል ላይ የምትገኝ መሆኗን ማጤን ያስፈልጋል። እናም ኢትዮጵያ የጀመረችው የዕድገትና የዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ሂደት ስኬታማ ሆኖ እንዲቀጥል፤ አስተማማኝ ሠላም የሰፈነበት ምህዳርን መፍጠር "ለነገ" የምትተወው ተግባር አይደለም፡፡ ለምን ቢባል፤ ለኢትዮጵያ ፈጣን ልማትን ማምጣትና ከተመጽዋችነት መላቀቅ "የሞት -ሽረት" ያህል የህልውና ጉዳይ ስለሆነ ነው፡፡

ስለሆነም የርዕዮተ-ዓለም አቀንቃኞቹ ፅንፈኛ ኒዮ-ሊበራል ሃይሎች "ቤተሰባዊ" ዜማ ሰሚ አልባ ቢሆንም፤ አንድን ጉዳይ ደጋግሞ በማዜም ሊመጣ የሚችል አንዳችም ለውጥ አለመኖሩን ማወቁ ማለፊያ ይመስለኛል። ለምን? ቢሉ፤ በተለያዩ ስያሜዎች እርስ በርሳቸው እየተጣሩ በአንድ ሀገር ላይ የአሉባልታ ዘመቻ መክፈት ከትዝብት በስተቀር የሚያስገኘው ፋይዳ ስለማይኖር ነው።

እናም "ቤተሰባዊ" ዘፈኑ በፈጣንና ተከታታይ ዕድገት ውስጥ በገባችው ሀገራችንን ወደ ኋላ ሊጎትታት አይችልም። በሀገራችን ህዝቦችና በመሪው መንግስታቸው የተያዘው ልማታዊና ዴሞክራሲያዊ የነብር ጭራ መቼም ቢሆን ሊለቀቅ የሚችል አይደለምና።